# ከግንቦት 10 እስከ 12ቀን 98ዓ.ም በኒዘርላንድ ሀገር በኡትረክት ከተማ ስለተካሄደው የተቃዋሚ ኃይሎች ስብሰባ የቀረበ ዘገባ

የኦሮሞ ነፃ አውጪ ድርጅት (ኦነግ) ያዘጋጀው ስብሰባው አርብ ግንቦት 10እስከ ግንቦት 12 ቀን 98 ተካሂዷል ፡፡ በስብሰባው ላይ የካፈሉት ድርጅቶች ስድስት ሲሆኑ እነሱም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

1ኛ. የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ( ዳውድ ኢብሳ - ሐሰን ሁሴንና ተማም ሁሴን)
2ኛ. ቅንጅት ( ሻላቃ ዮሴፍ - ሰለሞን በቀለ - ዶ/ር ሰዩም ሰለሞን እና አዳርጋቸው ፅጌ)
3ኛ. የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር ( አብዱር ቃድር-አብዱራህማን....)
4ኛ. የሲዳማ ነፃ አውጪ ግንባር ( ገልፈቶ ፌቃ- ቤተና ሆጤሶ- ሚልኪያስ ግልገሎ እና መንዛ መጌ)
5ኛ. የኢትዮጵያ ህዝቦች አርበኞች ግንባር ( መስከረም አታላይ- ስለሽ ጥላሁን እና ግሩም )
6ኛ ኢድኃን ናቸው ፡፡ (አረጋዊ በረሔ -ዶ/ር ነገደ ጎበዜና ዓቢይ ) በስብሰባው ላይ ከእያንዳነብዱ ድርጅት በቁጥር ሶሶት ሰዎች የተወከሉ ሲሆን ከቅንጅትና ከሲዳማ ነፃነት ግንባር አንድ(መንዛ መጌ) ከቅንጅት አንድ (አንዳርጋቸው ፅጌ) ታዛቢዎች በሚል መገኘታቸውን የስብሰባው አዘጋጅ ሊቀመንበር የሆነው የኦነጉ ዳውድ ኢብሳ ገልጿል ፡፡
7ኛ. በስብሰባው ላይ በይፋ በስብሰባው አዳራሽ እንዲገኙ ባይደረግም የኤርትራው ሻዕብያ ሰው አቶ የማነህና ሌሎችም በትንሹ በቁጥር ከአምስት እስከ ሰባት የሆኑ ሰዎች ስብሰባውን በቅርበት ይከታተሉ ነበር ፡፡ እንደአስፈላጊነቱም ለታሰተፉት ድርጅቶች ከኢዴኃን በስተቀር ምክርም - ዱለታም-ተክሳፅም- ትዕዛዝም በመስጠት ስብሰባው እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ከውጪ ሆነው በስልክ እና በአካል ክትትልና መመሪያ በመስጠትከፍተኛ ትብብር አድርገውላቸዋል ፡፡ የኡትረክቱን ስብሰ ከስብሰባው አደራሽ ውጪ- በማስተናገድ- በቅርበት በመከታተል- በመቆጣጠር ከፍተኛ ሚና ሻዕቢያ እንደነበረው በገሃድ የታየበት ታሪካዊ ተውኔት ነበር ለማለት ይቻላል ፡፡

ስብሰባው ከመጀመሩ አስቀድሞ የኢዴኃን ተወካዮች በተናጥል ከኦነግ ሰዎች ጋር እንዲሁም በጋራ ከተጋበዙት ድርቶች ተወካዮች ባሉበት ሰለስብሰባው አጠራርና አዘገጃጀት ላይ ያላቸወን ቅሬታ- ስሰብሰባው ትክክለኛ የአሰራር ሂደትን የተከታለ አለመሆኑን- ድብቅና አስቸኳይ መሆኑነን በጥሞና አስረድተዋል ፡፡ ከላይ በጠቀሱትም ምክንያቶች የተነሳ ማለትም ስብሰባው ግልፅነት የሚጎድለውና ሁሉም ድርጅቶች አስቀደመው አውቀውት- ሀሳባቸውን ልከው- በጋራ አጀንዳ ነድፈው- ለስብሰባው መንደርደሪያ ወይም መነሻ የሚሆን ህሳብ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ- በሥርዓት የተዘጋጀ አለመሆኑ ፡፡ ይህንንም በተመለከተ ኀብረቱ ደብዳቤ ለኦነግ ፅፎ እንደነበር ተገለጠ፡፡ ይህ ስብሰባ ፐሊምነሪ ስብሰባ ተደርጎ በኢዴኃን በኩል የሚወሰድ መሆኑን ለማስረዳት ተሞክረ ፡፡ የኦነግ ሰዎችም ግዴለም እንደፐሊምነሪ ብታዩትም ገብታችሁ ተሳተፉ በሚል ወደስብሰባው አዳረሽ እንዲገባ አደረጉ ፡፡ ቅሬታውንም ኢዴኃን ለተስብሳቢው በስብሳበው ላይ በይፋ ደጋግሞ ገለጠ ፡፡

የኦነጉ ዳውድ ኢብሳ የሊቀመንበርነቱን ሥፍራ ያዘ የኦነጉ የውጪ ግኑኝነት የሚባለው ሐሰን ሁሴን ቃላ ጉባዔ መያዝ ቀጠለ ፡፡ በእንኳን ደህና መጣችሁ የዳውድ ንግግር ከተደረገ በኋላ ኦነግ ለዚህ ስብሰባ መሳካታ ከተሳታፊ ድርጅቶች ጋር የተናጥል ግኑኝነት በማድረግ ከአንዳንዶቹ ጋር ከሶስት ዓመት በላይ ከሌሎቹ ጋር ደግሞ ከስድሰት እስከ ሰባት ወር የፈጀ የግኑኝነት ጥረትና ድካም ያደረግ መሆኑን ገለፀ፡፡ ከዚያም በመቀጠል ሁለት አጀንዳዎች እንዳሉ፡፡ ይህንን አጀንዳ የቀረፅነውም በስብሰባው ላይ በተናጥል ባደረግነው ግንኘነት ነው ሲል ገለጠ ፡፡ ይህንን ሀሳብ ከኢዴኃን በስተቀር ሌሎቹ ተሳታፊ ድርጅቶች እንዳለ ነበር የተቀበሉት ፡፡ በማስከተልም ዳውድ ኢብሳ ሁለቱን የአጀንዳ ነጥቦች ሰነዘረ ፡፡

1. ተጨባጭ ሁኔታን በተመለከተ (Assement of the current situation)
2. የተቃዋሚዎችን ትብብር በተመለከተ (The need for alliance) የሚሉት ነበሩ ፡፡

በቀጥታ ለመንደርደሪያ ለመግቢያ የኦነጉ የወጪ ኃላፊ የተባለው ሐሰን ሁሴን ሀሳብ እንዲተያቀርብ ሊቀመንበሩ ዳውድ ኢብሳ ይጋብዘዋል ፡፡

ሐሰንም በመቀጠል ፡- ይህ ስበስባ በአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል ብለም እንገምታለን ፡፡ እስካሁን ወያኔ የነበረው ድጋፍ በውጪው ኃይል ነበር፡፡ ራሱን ለማንገሥና አምባገነናዊ አጋዘዙን ለማጠናከር የተጠቀመበት ፡፡ ከ 2005ቱ የግንቦቱ ምርጫ በኋላ የመለስ አገዛዝን አጋልጧል ፡፡ እንዲነጠልም አድርጓል ፡፡ አሁን ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብም ለውጥ በአገሪቱ እንዲመጣ ይሻሉ ፡፡ ግን አማራጭና ጠንካራ ተቃዋሚ ኃይል ይሻሉ ፡፡ የወያኔ አገዘዝ ለውይይት ዝግጁ አይደለም ፡፡ ተቃሚዎች ይጋዛሉ - ይገደላሉ- ቅንጅቶችን በማዋከብ ላይ ይገኛል አገዛዙ ፡፡ ኦነግ ላይ ያለው ሽብር ይኸው እንደቀጠለ ነው ፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመቀየር አዲስ ጅማሮና የጋራ የሆነ ትብብር መፍጠር ጊዜው ይጠይቃል ፡፡ የግልና የጋራ የሰው ልጆች መብት እንዲከበር የህግ የበላይን እንዲሰፍን መታገል አለብን ፡፡ በ2005 ምርጫ ህዝቡ ድምፁን በመስጠት ዴሞክራሲያዊ መብቱን ለማስከበር ታግሏል ፡፡ ለፍትህ ተሰውቷል በተጨባጭብ አስመስክሯል ፡፡ ተቃዋሚው ከ1974ዓ.ም ጀምሮ በአገር ቤት ጫካዎች በውጪም ታግሏል፡፡ ለለውጥም ከፍሏል፡፡ ግን በኀወኃት ድሉ ተነጥቋል ሴል የኦነጉ ሊቀመብር ዳውድሀሳቡን ቋጨ፡፡

በማስከተል ዕድሉ የተሰጠው ለቅንጅት ተወካዮች ነበር ዶክተር ስዩም ሰለሞን፡፡ ባለፉት አሥራ አምስት አመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በህዝቦቿ ላይ ከፍተኛ ችግርና አዳጋ ተጋርጣል ፡፡ ይህ እውነታው ሆኖ ሳለ መለስ የአገሪቱ ኢኮኖሚ

እያደገ ነው ሲል ይደመጣል ፡፡ ዕውነታውን ስናይ ግን የአገሪቱ የግብርና ምርት ከኃይለስላሴ ጊዜ በባሰ ሁኔታ እያሽቆለቆለ ነው ፡፡ ከሀገራችን ህዝብ አርባሁለት ከመቶ የሆነው የቀን ገቢው ከአንድ የአሜሪካን ዶላር በታች ነው ፡፡ ሃያ ሁለት ከመቶ ብቻ ነው ንፁህ ውሃ የሚጠጣው ፡፡ መሬት በመንግሥት እጅ ነው ፡፡ ገበሬው ጭሰኛ ነው ፡፡ ገበሬው በግብር ስለተወጠረ ያለውን ንብረት ሁሉ እንዲሸጥ እየተደረገ ነው ፡፡ ሰባሰበት ከመቶ የሚሆነው ወጣት ሥራ አጥ ሆናል ፡፡ ወጣቱን አገዛዙ ወጣት ቦዘኔ በሚል ፈርጆታል ፡፡ ምንም ዓይነት የልማት ሥራ የለም ሰላም በሌለበት አገር በኢኮኖሚ ግንባታና ልማት ላይ እንሸሰት የሚያደርግ የውጭ ዜጋ የለም ፡፡ የሲቪክ ማህበራት ፈርሰዋል ፡፡ ጆሮ ጠቢው በዝቷል ፡፡ ሚዲያው በወያኔ ሥር ነው ፡፡ የቅንጅት. መሪዎች ታስረዋል ፡፡ ለሞት ቅጣት ተዘጋጅተዋል ፡፡ የውጪው ኃይል ተፅዕኖ እንዲያደርግ እየጠየቅን ነው፡፡ ዳሩ እነሱ ስላሰቀመጡት መለስን ሊያነሱት አይፈልጉም ፡፡ ከወጪ የምንጠብቀው ነገር የለም እኛው በእኛው ልዩነታችንን አቻችለን ትብብር (አላያንስ) በመፍጠር የመለሰን አገዛዝ ማስወገድ ይኖርብናል ፡፡ ያለን አማራጭ እሱ ሰለሆነ ለዚህ መሥራት ይኖርብናል ፡፡

.የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ተወካይ(ሊቀመንበር አብዱል ቃድር)፡፡ ባለፉት ዘመናት ሥናልብ የነበረው የፀረ - ዴሞክራሲና ፀረ- ፍትህአምባገነኖችን ምርት ነው፡፡ ጥፋትና መከራ ነው በአገራችን የተዘረጋው፡፡ ወደኋላ መለስ ብለን ስናይ መከፋፈላችን አብረን አለመቆማችን የመለሥን የሥልጣን ዕድሜ አራዝሞታል ፡፡ በኦጋዴን ብቻ ከስምንት ሺህ በላይ አስረኛ ያለ ሲሆን ግድያውም ያን ያህል ነው ፡፡ ዜሬም የኦጋዴን ህዝብ እየተጨፈጨፈ ነው ፡፡ መለሥ በተናጥል እየገደለን ነው ፡፡ በየተራ ህዝቡን እየነጣጠለ እየመታ ነው ፡፡ ምሥራቅ - ምዕራብ-ደቡብ አሁን ደግሞ መሃል (አማራውን እየመታ ነው ) በኦጋዴን አካባቢ የኬሚካል መርዝ እየጠቀመ ነው መለስ ህዝቡን ለማጥፋት ፡፡ ታሪክን እንለውጥ እላለሁ ፡፡

. የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባርሊቀመንበር መሥከረም አታላይ፡- ይህ ዕድል መገኘቱ ይጠቅማነል ፡፡ የአገራችንን ችግር መዘርዘሩ ብቻ በቂ አይመስለኝም ምን ይደረግ ነው ወናው ቁምነገር ፡፡ በሰላም ከነመለሥ የሚጠበቅ ነገር የለም ፡፡ እርስ በርስ የመከፋፈልና የመታኮሱ ጉዳይ ማብቃት አለበት ፡፡ የቅንጅት መሪዎች እስር ላይ ነው ያሉት ፡፡ አጋራችንን እንዴት እናድን ነው ዋነው ነገር፡፡ በፊት ያልነበረ በጎጥ መታየየት ይብቃ፡፡ ወያኔ የለም ዛሬ፡፡ ወያኔ ደክሟል ፡፡መሠረት የለውም ፡፡ ትብብር መሥርተን መታገልነው

.የሲዳማ ነፃነት ግንባር ለቀመንበር ም/ሊቀመንበሩ ቤተና ሆጤሶ፡- ሰለችገሩ መዘርዘር መፍትሄ አያመጣም፡፡ መለሥ በአራቱም ማዕዘን ይገድላል ፡፡ ይህን ለታሪክ ትተን ለወደፊቱ መሥራት ነው ፡፡ እኛ ያለፈውን ምርጫ አልደገፍንም ነበር ፡፡ መለስን ሰለምናውቀው ፡፡ ምን ሊመጣ እንደሚቺልም ውጤቱን እናውቀው ነበር ፡፡ በምርጫው የተሳተፉትም ከስህተታቸው የተማሩ ይመስለናል ዛሬ ፡፡ መለስ ዛሬ በውስጥም በውጪም ተጋልጣል ፡፡ ይህየዛሬው ትልቅ ጅማሮ ነው አብሮ ለመምጣት ፡፡ የነበረብንን ልዩነት ወደጎን ትተን ለአዲሰ ጅማሮ እንሥራ ፡፡ ዋናው ቁም ነገር መተባበርና በአንድ ላይ መቆም ነው-- አለበለዚያ መለስ እያጭበረበረና እየከፋፈለ ይቀጥላል ፡፡ አብረን ከቆምን ኃይል ይኖረናል፡፡ኢዴኃኑ ሬዘርቨሼን አለን ያሉ ቢሆንም ይመጣሉ ፡፡

.የሲዳማ ነፃ አውጪ ግንባር ሊቀመንበር (ገልፈቶ ፌቃ)
ለመሰባሰባችን ጥረት ያደረጉትን በቅድሚያያ ላመሰግን ይፈቀድልኝ ፡፡ ሁላችንም አንድ አይነት በሽታ ነው ያለብን ፡፡ ህዝባችን እየተሰቃየ ነው ያለው ፡፡ እኛ የህዝብ ወኪሎች ነን ፡፡ እስከዛሬ የነበረውን የአገራችንን ሁኔታ ለታሪክ እንተወው ፡፡ ይቺን ሀገር ይህንን ህዝብ መታደግ አለብን ፡- ይቺ አገር የጋራ እናታችን መሆኗን ማወቅ አለብን ፡፡ የጋራ ቤት ለመሥራት በጋራ መቀም አለብን ፡፡ ፖለቲካ ቋሚ ፎርሙላ የለውም ፡፡ ቦታ ሁኔታና ጊዜ ከተስተካከሉና በጎ አመለካከት ካለ ፖለቲካ መሥራት ይቻላል ፡፡ እነዙህ ሁኔታዎች የተሟሉ ናቸው ወይ ?ነው ወናው ጥያቄ፡፡ እዚህ የመጣነው ለመፈታተሽ ነው ወይስ የጋራ መፍትሄ ለመፈለግ ነው ፡፡ የእኔ እምነት ሶስቱም ተሟልቷል ነው ፡፡ ፍቃደኝነቱ ከታከለበት ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡ ከዚህ በፊት ብዙ የኅብረት ሙከራዎች ተደርገዋል ፡፡ከፓሪስ አንድ ጀምሮ እስከዛሬ፡፡ የሰውና የገንዘብ ኃይል ባክኗል፡፡ አብዛኛዎቹ ፈርሰዋል፡፡ ይሄ የዛሬ የመጨረሻው ይመስለኛል ፡፡ ለሞት የተቃረበውን ወያኔን ለመቅበር ካልቻልን እኛው ነን የሞትነው ፡፡ እባካችሁ በጋራ እንሥራ ፡፡ አማራና ኦሮሞ አይስማሙ እያለ መለስ እየቀለደብን ነው ፡፡ የውጪው ማህበረሰብ ጆሮን እንዲሰጥ መሰባበሰብ አለብን ፡፡

ዳውድ ሁላችንም አንድ ቋንቋ ነው የምንናገረው

አረጋዊ - የመለስ አገዛዝ አምባ ገነንና አሸባሪ አገዛዝ ነው ፡፡ በግንቦቱ ምርጫ ብናይ የሚያሳየን ህዝብና ተቃዋሚው ባንድ ላይ ተገናኝተው ለውጥ ፈልገው ለለውጥ ተነሱ ፡፡ ዬሮለፈውን ታሪካችንን ብናይ ከአንድ አገዛዝ ወደሌላ ነው የተሸጋገርነው እንጂ ለውጥ በአገራችንእንዲሁም ለህዝባችን አልመጣም ፡፡ በህዝብ የተመረጠ ለህዝብ የቆመ ሥርዓት እስከዛሬ አልተመሠረተም ፡፡ የኡጋዴኑ ተወካይ አቡዳህማን እንዳለው አዲስ መንፈሥ ይዘን መነሳት መከበባር መቻቻል -እንደሰው ልጅነታችን የሰው ልጅን መብት ማክበርን የሚጠይቅ ይመስለኛል ዋነው ቁም ነገር ፡፡ አገራዊ ችግራችንን ለመፍታት መሠረታዊ የሆነዩ ነገሮች ያሻሉ ፡፡ ለዚህም መሠረቱ ዲሞክራሲ ነው ፡፡ ህዝባችን ዛረም ሆነ ነገ ምን እንደሚሆን ? ምን እንደሚመጣበም/ ወይም እንደሚመጣለት አያውቀም ፡፡ አደጋና ጨለማ የሆነ ጭጋግ አየዘነበ ነው በአገራችን ፡፡ ከዚህ ሁኔታ ለመውጣት በጋረ መቆም በጋረ መተባበር ይገባናል፡፡ ይህ ዕውን ሲሆን ነው መለስ ሊወገድ የሚችለው ፡፡ በውሸትና በንዋይ ላይ የተመሠረተ አገዛዝ ነው የመለሥ አገዛዝ ፡፡ መለሥ አምባገነን ነውና የትግራይ ሕዝብ ድጋፊ የለውም ፡፡ ህዝቡ የእቅሮን የተቃዋሚዎችን እውነተኛ ትብብር ይጠይቃል ፡፡ ሰለዚህ በጋር መቆም አለብን ፡፡ ለዚህም ሁሉም የተቃዋሚ ድርጅት የእኔ ነው የሚለው ህዝቡም የሚደግፈው ኅብረት መመሥረት የኖርብናል ፡፡ ቋሚ የሆነ ህዝባዊ ህገ-መንግሥት ባለሞሩ እስከዛሬ ድረስ ከዚህ አዙሪት ለመውጣት ያልቻልነው ፡፡
ዳውድ ፡- ህዝቡ አረጋዊ እንዳለው የሱ የሆነ ህገ-መንግሥት የለውም ፡፡
ሀሰን ሁሴን፡- ሁሉንም ተቃወሚ አንድ ላይ ለማምጣት ሞክረናል ፡፡ ዛሬ ከተሰባሰብን ታሪክ እንሰራለን ብዬ አምናለሁ ፡፡

ይህ የዛሬው ታሪካዊ ጉባዔ ነው ። አደራ እላለሁ የኅብረቱን ተወካዮች ። በሚቀጥሉት ሰዓታት ከኅብረቱ የአቋም ወይም የውሳኔ ለውጥ እንጠብቃለን በጋራ ኅብረት ለመመሥረት።
ዳውዲ፡-ፀ ይህ ዛሬ ያሰባበሰን የረዥም ጊዜ አጀንዳ ነው። በአ?ኛ በኩል ለምንድነው እስከዛሬ ድረስ ፈሬ ያፈራ መሰባሰብ ያለተደረገው ። ኅብረት የምንፈጥረው የወጪው ማህበረሰብ ሰለሚጠሥ/ቅና ግፊት ሰለሚያደረግ ነው ?፡ወይስ ለይስሙላ ሲባል ነው መሰባሰቡ ወይስ ለውጥ በጋር ለማምጣት ነው የሚለው ነው ፈታኙ ጥያቄ። ህዝባችን ምን ይጠይቃል ?። ምንስ ከተቃሚው ይጠብቃል?። ቀደም ሲል እንዳየነው የተለያዩ ኅብረቶች ተፈጥረዋል ፍሬ አላፈሩም እንጂ። የአሁኑ ለውጥ የሚያመጣ ፍሬ የሚያፈራ የህዝብ ጥያቄ የሚመልስ መሆን ይገባዋል ።
ሀሰን፡- በዚህ ጉባዔ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ድርጅቶች የተሰባሰቡበት ነው። ሰለዚህ የምንፈጥረው ትብብር (አላያንስ ) ለህዝባችንም ለውጪው ማህበረሰብም ትክክለኛ ምላሽ የሚሰጥ መሆን ይገባዋል ። ነው የምንለው ።

አረጋዊ ፡- ይህ አጀንዳ ወደጠረጴዛው ተወርውሯል በእኛ እምነትአላይንስ የሚለውን ለመግፋት በቅድሚያ ያለፉትን ኅብረቶች በመገምገም መነሳት አለብን ። ለምን የቀድሞዎቹ አልገፉም ፍሬ አላፈሩም የሚለውን ማየትና መመርመር መልስ ሰጥተን ካልሄድን ለዚህስ ምን ማስተማመኛ ዋስትና አለን? ለማየት ይረዳናል ። ይህንን ካየን ከስህተት ተምረን አስተማማመኝ የሆነ ዘላቂ ህብረት መመሥረት ይቻላል ። መግለያ ባቻ ማየቱ የትም አያደርሰንም ። እንደምሣሌ የምጠቅሰው ኅብረቱ የሲቪክ ማኅበራት - የሚያ ማኅበራት እንዲሳተፉበት እንፈልጋለን በሚፈጠረው ትብር (አላያንስ ) ። ህዝቡ የእኔ ኅብረት ነው ብሎ እንዲነሳ። ለዚህም ነው ይህንን ሀሳብ ለኦነግ ኅብረቱ አንስቶ የነበረው ። ይህን ተመሳሰይ ጥያቄ(ሀሳብ ) ለቅንጅትም አንስተን ነበር ። ደብዳቤም ለሁለቱም ዕፈናል። ሁሉን አቀፍ አገራዊ ጉባዔና የቀውጢ ጊዜ ግብረኃይል እንዲቋቋም። ይህ ነበር የኅብረቱ ጥሪት። ይህ ጥሪ ለምን ምላሽ እንዳላገኘ ለእኛም ግልፅ አይደለም እስካዛሬ ድረስ ። በአጣቃላይ ይህ ነው በግልፅ የኅብረቱ ዓላማ። በእኛ በኩል ለትብብርና ለኅብረት እንቆማለን። ግን በአሁኑ አካሄድ ላይ ልዩነት አለን። ግልፅነት ይጎድለዋል ። የዚህ ጉባዔ ውጤቱ እንዲያምር ከተፈለገ ይህ ጉባዔ የቅድመ ሁኔታ ወይም የዝግጅት ( ፕሊሚነሪ) ስብሰባ ተደርጎ መወሰድ አለበት ነው የምንለው እንደኅብረት።
ዳውድ፡- ይህንን በተመለከተ ከኅብረቱ ጋር በግል እናወያየለን ። አሁን ግን ሥራውን በዚህ መድረክ መጀመር አለብን ። በእኛ በኩል መድረኩን ሳናሰፋው እንጀምር ትብብሩን ነው የምንለው ።
ዳውድ፡- አሁን ያሉት የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ከድርጅቶች ተፅዕኖ ነፃ አይደሉም ። የድርጅቶች ተለጣፊዎች ናቸው እናውቃቸዋለን ። የትኛው ነው አሁን ነፃ ማህበር የሚባለው? ውስጥ ያለው ነው ወይስ ውጪ ። ውስጥ ያለው የተከፋፈለና በወያኔ ቁጥጥር ሥር ያለ ነው ። ውጪ ያለው በፖለቲካ ድርጅቶች ተፅዕኖ ሥር ያለ ነው ። በእኛ በኩል አሁን አላያንሱን ፈጥረን ወደፊት በሚደረገው አገራዊ ጉባዔ ሁኔታውን እናየዋለን ። ሰለዚህ አሁን የምንፈጥረው የፖለቲካ ድርጅቶች አላያንስ ነው ።

አብዱራህማን (ከኦጋዴን) አላያንሱ እንደተባለው በዚህ መድረክ መፈጠር አለበት ነው የምንለው እኛም። ጥሪያችንን ለኅብረቱ ተወካዮች ነው የምናቀርበው አቋማቸውን ቀይረው በአላይንስ ምስረታው እንዲሳተፉ ። በእኛ አካባቢ በኦጋዴን ከፍተኛ ችግር አለ ። ጦርነት እየተካሄደ ነው ። ቻይናዎቹ ነዳጅ ለማውጣት ሰለሚፈልጉ መለስ በአካባቢው ሽብር እየፈፀመ ነው ያለው ነዋሪውን በመጨፍጨፍ። የቅንጅት መሪዎችም በእስር ላይ ነው ያሉት ። እነሱ እንኳን መሪዎቻቸው ታስረው በችግር እያሉ ለአያንሱ መፈጠር እየተባበሩ ንው ያሉት ። የኦጋዴን ህዝብ እስከዛሬ የተገፋ ህዝብ ነው ። የት እንደለን የማንታወቅ የተናቅንና የተጠላን ህዝቦች ነን። ኢትዮጵያዊነ ነኝ ለማለት ይቀፈኛል ። አሁንም የምናሳሰበው እባካቸሁ ቅንጅትና ኅብረትን ነው የማሳሰበው እናንተ አማራ ወንድሞቻችን አንድ ላይ እባካችሁ ኑ ። ዛሬ አላያንሱን ብንመሰርት ይጠቅመናል ። በተለይ የኢሕአፓ ወድሞቻችንን እንማፀናለን ።

ቤተና ሆጤሶ (ሲዳማ) የአላይናስ መፈጠር በጣም አሰፈላጊ ነው ። አኛ እንፈልገዋለን ። በላመተባበራችን ጠላት እየከፋፈለን ነው ። ተመልከቱ ቅንጅትን እየከፋፈሉ እያዳከሙት ነው ። ዋናው ጥያቄ እንዴት አላያንሱን እንመሥርት በሚለው ጥያቄ ዙሩያ ላይ ነው ማተኮር ያለብን ።

ሐሰን(ኦነግ ) የጋራ ጠላት አለን። ኅብረት ያስፈልገናል ። መለስተኛ ፕሮግራም ላይ ተስማምተን ተማምነን መነሳት አለብን ። በነፃ የመንቀሳቀስ መብታችንን በአገራችን ለማስከበር ። በዕርዮት እንኳን ብንለያይ የጋራ ጠላት ሰላለን መተባባር አለብን ።የተሰባሰብነውም ለዚህ ነው ።
ዳውድ (ኦነግ )፡- ይህ ሃሳብ እንዲጠቃለል የሁሉም ፈቃደኝነት ያሻል ። ዝግጁነትን ይጠይቃል። በድርጅቶች በኩል። መቻቻል ያስፈልጋል በመካከላችን። የተለያየ የፖለቲካ ፕሮግራም እንዳለን ታውቆ። ምናልባት ልዩነት ቢኖርም ጊዜና ቦታ ለይቶ ማንሳት ይገባል ። ግባችን ምንድነው?። የኛ ግብ ሁሉን አቀፍ መድረክ ለመፍጠር እና ሌሎቹን በሂደት ለማምጣት ነው ። አላስፈላጊ ጥላችን በመካከላችንም ሆነ በህዝብ መካከል እንዳይነሳ መከላከል አለብን ። ለዚህም ፈቃደኝነትንና ቁርጠኝነትን ይጠይቃል ጊዜው አሁን ነው ።
አንዳርጋቸው (ቅንጅት ) ግባችንን ሳንነድፍ ወደአላይንስ ለመፍጠር ለምን እንቸኩላለን ?።
አብዱራህማን(ኦጋዴን) ጥያቄ ለኅብረቱ ተወካዮች ነው ። እባካችሁ ሁኔታውን እንደገና እዩት በሚገባ ይህንን ትብብር (አላይናስ) እንፍጠር ።

አረጋዊ፡- የእኛም ዓላማ ትብብር /ኅብረት እንዲፈጠር ነው ፍላጎታችን ። አላያንስ ስንል ትብብር ወይም ኅብረት ስንል ዓላማው ምንድነው። እንዴትስ ነው መፈጠር ያለበት በሚለው ላይ ነው ልዩነታችን እንጂ በጋራ መቀም አለብን በሚለው ላይ ምንም ብዥታ የለብንም በዚህ ላይ በምንም መንገድ ጥርጣሬ ወይም በሌላ መንገድ እንዳያቱ ነው እኛም አደራ የምንለው ።
የአርቡ የሜይ 19 ስብሰባ ከላይ ባሉት ውይይቶች ተጠናቀቀ ። በኅብረቱ በኩል ኅብረቱ እንዴት ወደ ኡትረክቱ ጉባዔ

/ስብሰባ እንደመጣ በሚገባ በተወካዮቹ አማካይነት ለተሰበሰቡትም ሆነ ስብሰባውን ላዘጋጀው ለኦነግ ሰዎች ተነገራቸው :: ልዩነታችንንም በስብሰባው አካሄድ ላይ አሰረዳን :: በእነሱ በኩል ግን ፈጥኖ አላያንስ የሚለውን መፍጠር በጣም አስፈላጊና ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑን መግፋት ያዙ ኦነጎቹም ሆነ በስብሰባው ላይ የተካፈሉት ድርጅቶች በጠቅላለው :: ትንሽ ሪዘርቬሽን የሚታይ የነበረው ከቅንጅቱ ከአዳንዳርጋቸው ፅጌ/ በኩል ነበር ::እሱም ገፍቶ ሊቃወማቸው አልሞከረም :: የተቀሩት ሙሉ በሙሉ የኦነግን ሃሳብ ነበር የሚገፉት :: በዚህ መሃከልም የሻዕብያ ሰዎች በአካባቢው ይታዩ ነበር የማነህን ጨምሮ ::

<u>ቅዳሜ ግንቦት 20</u>

ዛሬም ሊቀመንበርነቱን የኦነጉ ዳውድ ኢብሳ እና ፀሃፊው ሀሰን ሁሴን መድረኩን እንደያዙ ቀጠሉ :: በደንህና አደራችሁ ዳውድ ስብሰባውን ከፈተና ሁለት የኢትዮያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተወካዮች መገኘታቸውን ገልጠ:: አስተዋወቅ እነሱም ግሩም ግርማና ስለሺ ጥላሁን ይባላሉ :: ሁለቱም የፖለቲካ ኃላፊ መሆናቸው ተነገር :: ስበሰባው ቀጠለ ::ለማጣራት እንደተሞከረው ሁለቱም ለደን የሚኖሩ ወጣቶች ናቸው ::

ዳውድ :- የኅብረቱ ተወካዮች አዲሲ ሀሳብ ይዘው መጥተው ከሆነ ጠየቀ :: በኅብረቱ በኩል በግልጥ አሁንም ያለን አቋም ግልፅ ነው በአላያንስ ምሥረታው ላይ ችግር የለብንም :: ቀደም ሲል እንዳናሳነው እንዴት ወዴት በምን መልኩ በሚለው ላይ ግልጥነት መኖር አለበት ነው የኅብረቱ አቋም :: ይህንን ቀደም ሲል በቃልም በደብዳቤም ገልጠናል በሚል ዳም ተገለጠ ::

ዳውድ' ስለአላያንሱ ምሥረታ በኦነግ የተዘጋጀ ሰንድ አለና ታዩታላችሁ ሀሳብም እንለዋወጥበታለን በሚል ሀሳብ ሰጠ:: ሁለት ሰነዶችም ታደሉ በአንድ ሰዓት ውስጥ ሰነዶቹን አይቶ ሀሳብ ይዞም እንዲመጣ በዳውድ አብሳ ተሰጠ ::

ዶ/ር ነገደ (ከኅብረት ):- የትብብሩ (የአላያንሱ)ዓላማ መሆን ያለበት የሽግግር ዘመን ለማምጣት ነው የኛ ትግል እዛ ለመድረስ ነው ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ይጠራ የምንለው :: ሽግግሩን ለማሳካት ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ማድረግ ነው :: ይህም የሚሆነው በህዝባዊ ትግል ነው :: የህንን ፍሬአማ ለማድረግ ሁሉን የኅብረተሰቡን ክፍል ማሳተፍ ያስፈልጋል:: (የሲቪክ መኅበራት-የሙያ ማኅበራት ን ወዘተ ) የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አውጥቲቅ ህዝቡን ማንቀሳቀስ ይገባል ማለት ነው :: አላያንስ ከፈጠርክ :: ይህ አላየንስ ዲሞክራቲ የሆነ ሽግግር እንዲሳካ የሚሰራ ነው :: ሽግግሩም ተሳካ የሚባለው አጋራችን ውስጥ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ተደርጎ ሽግግሩን ተግባራዊ የሚያደርግ ኅብረቱ ባቀረበው ሰነድ መሠረት የሚሰራ ዴሞክራቲያዜሽን ካውንስልና ብሔራዊ እርቅ ጉባዔን ተግባራዊ የሚያደረግ ኮሚሽን ያቋቁማል ማለት ነው :: እዚህ ላይ ሲደርስ አላያንሱ ጊዜው ያበቃል:: እዚህ ለመድረስ ኢህአዴግን በህዝብ ትግል ማስገደድ ብቻ ነው አማረጩ:: በግልፅና በደንብ በሁሉም ተሳትፎ ከጅማሮው ያልተመሰረተ አላያንስ ከሆነአስቸጋሪ ነው :: በግልፅና በሁሉም የተደገፈ አላያንስ ትብብር ከሆነ ::ይህንን ህዝባዊ ትግል በጠቅላላው የህብረተሰቡ ክፍል የሚደግፍ ይሆናል:: ሰለሆነም አዲስ አባበ ውስጥ ጉባዔውን ጠርቶ አላያንሱን ማስፋትም ያስፈልጋል :: ይህንን ጉባዔም ለማሳካት ከወዲሁ አንድ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚሽን ከሁሉም የኅብረተሰቡ ክፍል የተውጣጣ እንዲያስተባብረው ያስፈልጋል ::

ሀሰን(ኦነግ ) ወደሰነዱ እንመለስና በሰነዱ ላይ ሀሳብ እንዲሰጥበት በኦነግ ተዘጋጅተው የቀረቡ ሰነዶች ለተሳታፊዊ ታደሉ ::

1.Memorandum of Understanding for Freedom and Democracy

2.Statutes of the Allaince for Freedom and Democracy የሚሉ ነበሩ እነዙህ ሁለት ሰነዶች በኦነግ ተዘጋጅተው ይቀረቡ ይባል እንጂ ከኢዴኃን በስተቀር ሌሎቹ ቀደም ሲለን ያዩዋቸውና በዝግጅቱም የተሳተፉባቸው ለመሆናቸው በሰነዶቹ ላይ በተደረገው የውይይት ወቅት ለመረዳት አላሰቸገረም :: በመሆኑም በጠቅላለ በኦነግ ቀረበ የተባለውን ሰነድ አሁንም ከኢዴኃን በስተቀር ጠንከር ያለ የማሻሽያ አና የተቃውሞ ሀሳብ ያቀረበ ድርጅት አልነበረም ቅንጅትን ጨምሮ ::

አረጋዊ (ከኅብረቱ ) በአጠቃላይ በአላያንሱ ምስረታ ላይ ይህ አላያንስ ማተኮር ያለበት ሁሉንም ያቀፍ ስብሰብ እንዲሆን ነው የኅብረቱም የፀና አቋም ይሄው ነው :: ሰለሆነም ወደፊት አገራችን ውስጥ ለመፍጠር ለምናስበው የዴሞክራሲ መሠረትም ይረዳል :: ሰለሆነም ሁሉንም ለማምጣት አንድ ስልት መንደፍ ያስፈልጋል :: ለዚህም ነው ኅብረቱ ሁሉን አቀፍ ብሎ የሰየመው :: ይህ ደግሞ ሁለት ነገሮችን የተመረኮዘ ይሆናል :: በሰላምና በትጥቅ ገዥውን ቡድን የሚፋለሙት መሆኑ ነው :: እንደ እኛ ሁለቱንም ወገኖች አስተባበሮ ማስኬድ ይቻላል የሚል እምነት አለን :: ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በሀገራችን ለማምምጣት :: ሰለሆነም ሁሉንም የማሰባሰቡ ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል :: ለዚህም አንድ አሰባሳቢ ኮሚሽን ማቋቋምና ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል :: የሚል እምነት አለን :: ይህ ግባችን ከሆነ ሌሎች ኃይሎችን ማሰባሰብ ይገባል ::የሲቪክ እና የሙያ ማኅበራትን ማካተት ተገቢ ነው :: ህዝቡ የራሱን መብት እንዲያስከብር ያሻል :: ይህ ሁሉን የቃፈ ጉባዔም አገራችን መዲና እንዲደረገ እንታገላለን :: ያኔ ም የህዝቡን ድጋፍ እናገኛለን:: ህዝባችንንም በቀጥታ ለማንቀሳቀስ እንችላልን::

ዳውድ ኦነግ):- አንዴት እንሂድ ነው የምትሉት በአቀረብነው ሰነድ ላይ በሚል በጥያቄ መልክ ለቤቱ አቀረበ ::

ዶ/ር ነገደ (ኅብረት ) :- ማብራራያ ልስጥ ኅብረቱን በተመለከተ ፡ በአምስት ነጥቦች ማስቀመጥ ይቻላል ራዕያችንን ::

1. የሽግግር ጊዜ ዘመን አላይናስ ለማቋቋም ነው መባል ያለበት
2. ሁሉን አቀፍ ጉባዔ በአገራችን ለመጥራት ነው ዓላማችን
3. ዴሞክራታይዜሽን ካውንስል እና የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን/ካውንስል ለማቋቋም
4. ይህ ትግል የፖለቲካ ድርጅቶች ትግል ብቻ አይደለም የሙያ ማኅበራትናና የሲቪክ ማህበራትን-የሴቶች የወጣቶች ወዘተ ያካተተ ውጪ የምናደረገው ኮንፍረንስ ማለት ነው :: ይህ የመጀመሪያው ኮንፍረንስ የአላያንሱን ቤዝ ማስፋት-አመራሩን ማስፋት- ይገባዋል ማለት ነው ::የተለያዩ የኅብረተሰቡን ክፍሎች በማሳተፍ ህዝባው ትግሉን ለማጎልበትና አገዛዙን ለመወጠማ/ ያስቸለዋል አላዩንሱን ማለት ነው::
5. ይህ አስከሚጠራ ድረስ ህዝቡን ለትግል ማነሳሰት ይገባል:: የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ይፈቱ :: ነፃ ሚዲያ

ይኑር -ገዳዮች ለፍርድ ይቅረቡ- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይመሥረት ወዘተ በሚል በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ማሰለፍና መናሳሰት ይገባል ። የግንቦቱን ድል ለማስመለስ።

አብዱራህማን (ኦጋዴን ) እንዴት ነው አገር ቤት የምንለው የመለስ አገዛዝ ይህንን መቼ ይፈቅዳልና ነው ?

ነገደ (ኅብረት ) ይህ ማለት ነገ አገር ቤት እንግባ ማላት አይደለም የመለስን አዛዝ በተባበር ህዝባው ትግል እንወጥረው፡ በትግል በአመፅ ወደጠረጴዛ ዙሪያ እንዲመጣ ማድረግ ማለት ነው ።
ዳውድ(ኦነግ):- መጀመሪያ ጠላትን እናስወግድ ከዚያ የሽግግር ጊዜ የአደራ መንግሥት ወዘተ የሚሉ አሉ እሱ ወደፊት የሚታይ ነው ። እኛ የምንለው በትጥቅ ትግል ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች እናሰባሰብ ነው ። የሲቪክ ማህበራት አሰቸጋሪ ነው ለማሰባሰብና ወደዚህ ላምጣት ። እነዚህ ማህበራትበ ነፃ አይደሉም የተከፋፈሉም ናቸው። ሁሉም የፖለቲካ ድርጅት የራሱ የሆነ ተላጣፊ ማህበራት አሉት ኦሮም የራሳችንን ልናመጣ ነው ሌሎችም እንዲሁ ። ይህ አሰራር አስቻጋሪ ነው የሚመስለን ። የፖለቲካ ድርጅቶቹ ከተሳተፉ እነሱ እንደተሳተፉ ነው የሚቆጠረው።

ቤተና(ሲዳማ) ይህ የሲቪክ ማህበራት የሚባለው በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው የሚመስለን። ከመንግሥት ጋር የሚሰራ አለ ። የፖለቲካ ድርጅቶች ተቀጥላ የሆነ አለ ። ለምሳሌ የሰብአዊ ርጅት የተባለውን ብንወሰድ ነፃ አይደለም ። ሰለዚህ እሱን ለጊዜው እናቆየውና እኛ አልያንሱን እንመሥርት ።

ዶ/ር ስዩም(ቀንጅት ) ይህ በኅብረቱ የተነሳው ሃሰብ በጣም የሚደገፍ ነው ። ያለእነርሱ ተሳትፎ የትም አይደረሰም ። ይህ አላያንስ በሚያደረገው የሥራ ምደባ ላይ ምን ምን ይሥራ በሚለው አካሄድ ልናየው እንችላልን ። አሁን ግን ዋናው አላያንሱን መፍጠሩ ላይ ነው ። ለአለም አቀፉ ማህበረሰብም ሆነ ለህዝቡ አንድ ላይ መቆማችንን ማሳያት አለብን ። ህዝቡ ከዚህ ስብሰባ አንድ ነገር ይጠብቃል ። ሰለዚህ አደራ የምለውና ጥሪዬን የማቀርበው አንድ ቁም ነገር ሰርተን እንውጣ ነው ።

አንዳርጋቸው (ቅንጅት) አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንዳይሆን። ይህ አላያንስ ይመስለኛል ኢትዮጵያን ሊያድናት ሊገድላትም የሚችለው ። ሰለዚህ በኅብረቱ በኩል የተነሳው ህሳብ ተገቢና ትክክል ነው.። በምንም መልኩ የሲቪክ ማህበራትን ማስወገድ አይገባም ።

ዳውድ( ኦነግ ) በመጀመሪያ የፖለቲካ ድርጅቶች ሥራውን እንጀምር። አሁን ጊዜም የለንም ። ሌላው እንዲመጣ አላያንሱን እንፍጠር
ሚሊኪያስ (ከደቡብ ) የሲቪክ ማኅበራት ጉዳይ ለጊዜው ይቆይ ።
ህሰን(ኦነግ ) በዚህ ሰነድ ውስጥ የኅብረቱን ህሳብ ለማጠቃላል እንሞክራለን ወደፊት የሚታይ ጉዳይ ይሆናል ። አሁን ግን አላያንሱን መፍጠር ነው ዋነው ዓላማችን እዚህ የተሰባሰብነው ለዚህ ነው ።
አረጋዊ(ኅብረት ) በዚህ ሰነድ ዓላማ ላይ ግልፅ መሆን አለብን። ዋናው ነገር ለለውጥ ህዝቡን ማለጋጀት ይገባናል ። በሰላማዊና በትጥቅ ትግል ይህን አገዛዝ ማስወገድ ይቻላል ። በሁለቱም መንገድ ለመታገል ህዝቡን በግልፅ ማሳታፍ ይገባል ። ዋናው ጠቃሚው ነገር ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ማቋቋም ለትግሉ ዋልታ ነው ።
አብዱራህማን (ኦነግ ) በቅድሚያ እኛ አላያንስ ነው መፍጠር ያለብን። ከዚያ ሌለውን ሥራመሥራት ይቻላል ። የአላያንሱንም የመግባቢያ ቋንቋ እንግሊዘኛ ቢሆን የብሔር ብሔረሰቦች መብት አስከመገንጠል የሚለውም ቢገባ በሰነዱ ላይ የሚል ህሳብ አለን ። በእኛ በኩል ብዙ መንገድ ተጉዘን ነው በዛሬው ስብሰባ ላይ ከእናንተ ጋር ለመቀመጥ የበቃነው ።
(ኅብረት) የመገባቢያ ቋንቋ የሚለው አማርኛ ኦሮምኛ አንግሊዘኛ ሌሎችም በአገራችን በሚነገሩ ቋንቋዎች ጭምር መሆን ይኖርበታል ።
የቅንጅቱ አንዳርጋቸውና የአርበኞቹ ስለሽ መግባቢያ ቋንቋ አማርኛ ቢሆን በሚል ህሳብ ሰጡ።
ዳወድ (ኦነግ ) ይህን ጥያቄ አናንሳው ዛሬ ። ይህ ከተነሳ ብዙ የምንለው ይኖረናል። እዚህ ወስጥ አንግባ ከገባን ሌለ ችግር ውስጥ እንገባለን በቁጣ። እንግሊዘኛ እንደመግባቢያ ቋንቋ ሊሆን ይችላል ።
አረጋዊ -- ለመግባቢያነት ሁለቱንም ቋንቋ ብንጠቀም አማርኛና እንግሊዘኛ ።

/አብዱራህማን(ኦጋዴን) አማርኛ ቢባል ይጎዳናል ብለን ነው የምናሰበው በእኛ በኩል ።
አንዳርቻው (ቅንጅት) ሁላችንንም የሚያገናኝ ቋንቋ አማርኛ ነው። ሰለዚህ አማርኛ እንግሊዘኛና ሎችምንም መጨመር ይቻላል ብንልስ ።
ቤተና (ሲዳማ) እንግሊዘኛ በዋናነት አማርኛ እና ኦሮምኛ በሚለው ብንሄድ የተሻለ ነው ።
በቀረበው ሰነድ ላይ የተደረገው ውይይት እንዳበቃ በዳውድ አማካይነት በእስታቱቱ ላይ አነጎቹ ባቀረቡት መሠረት ስለአያሱ የሥራ ክፍፍልና የአላያንሱን ቢሮ በተመለከተ ውይይት ተጀመረ ።
ዳውድ (ኦነግ ) በሰነዱ ላይ እንደሰፈረው አላያንሱ ሰባት የሥራ አስፈፃሚ አባላት ይኖሩታል ይህንን በተመለከተ ነገ እሁድ ሜይ 21 እንቀጥላለን እኛ ሌላ ሥራ ስላለን ከዚህ በላይ መቆየት አንችልም በማለት ዳውድ የዕለቱን ስብሰባ አበቃ ።

ማምሻውን የኦነግ ተወካዮችና የቅንጅት ተወካዮች ። በዕራት ላይ አልተገኙም አንደገመትነው ከሆነ ሌላ ስብባ ወጣ ብለው ከሻዕቢያው የማነህ ጋር ስለስብሰባው ሂደት ለመወያየትና መመሪያ ለመቀበል እንደሄዱ ገምተናል ። አመሻሽተው የቅንጅትና የኦነግ ሰዎች የሻዕብያው የማነህ ጭምር ማምሻውን ተመልሰው መምጣታቸውን አረጋግጠናል

:: ከቅንጅቶቹ ጋር አንዳርጋቸውን አብሮአቸው አልሄደም ነበር ::

እሁድ ሜይ 21

ዳውድ ዛሬ ስብሰባው መጠናቀቅ እንደሚገባው ሀሳብ በመስጠት በሊቀመንበርነቱ ቀጠለ በሰነዱ ላይ የወያኔን ህገ መንግሥት አስመልክቶ ሀሳብ ተሰነዘረ በኅብረቱ በኩል :: የግንቦቱን ምርጫ ውጤት የህዝብ ድምፅ ይከበር- ለሽግግር ሥርዓት እንታገል የሚሉትና ሌሎችም በእኛ በኩል ልናነሳቸው የምንፈልጋቸው በርካተ ጠቀሚ ሀሳቦች በዚህ ሰነድ አልተካተቱም :: ህዝቡን እናደራጅ እናነሳሳ ስንል ይህንን ሥርዓት እንለውጥ ማለታችን ነው :: ሰለዚህ የወያኔ ህገ መንግሥት አብሮ መቀየር አለበት ነው የምንለው:: የወያኔ ህገመንግሥት እስታሊናዊ ነው የምንልው::

ዳውድ ቅንጅትና ኅብረቱ በምርጫው በህገመንግሥቱ ሥር ተሳትፋችሁ የለም ወይ ?:: ቁም ነገሩ ይህንን ህገ-መንግሥት መቀበል አለመቀበል ሳይሆን ዋናው ነገር ምን ለማድረግ ነው የምንፈልገው የሚለው ነው :: በእኛ በኩል ይህንን ያለውን ህገመንግሥት ተቀብለን መነሻ አድርገን ነው መሥራት ያለብን:: የሚሻሽል ካለ ወደፊት የሚታይ ነው :: አለበለዚያ ሀገሪቱን ማተራመስ ነው የሚሆነው :: ሰለዚህ ነው እኛ ይህንን ህገ-መንግሥት መሰረት ይዘን ነው መጓዝ ያለብን የምንለው :: አለበለዚያ አደጋ ነው :: ይህንን ሀሳብ ሁሉም ይጋሩታል ከኅብረቱ በስተቀር ::

ዶ/ር ስዩም ሰለሞን የዳውድን ሀሳብ እንጋራለን በዚህ ህገ- መንግሥት ሥር ተሳትፈናል ተቀብለናል ወደ ምርጫም ገብተናል አሸንፈናል ግን ከዚያ በኋላ ለመሄድ ስንሞክር ታግደናል

ዳውድ' ችግሩ ህገ መንግሥቱ አይደለም የወያኔ መንግሥት እንጂ::

ነገደ :- በግንቦቱ ምርጫ ተሳትፈናል አዎ ይህ ማለት ይህንን እስታሊናዊ ህገ መንግሥት ተቀብለናል ማለት አይደለም:: አሮ የምንለው መቀየር አለበት ነው:: ዋናው ትግላችንም መንግሥት ለመቀየር ብቻ ሳይሆን የህዝብ ያልሆነ ህገ መንግሥትንም ለመቀየር ነው ::

አረጋዊ - ይህንን ህገ መንግሥት ከተቀበልን በዚህ ህገ መንግሥት መገዛት አለብን ማለት ነው :: መለሥም የሚለን ያለው ህገመንግሥቱን ተቀበሉና ገብታችሁ ተንቀሳቀሱ ነው የሚለው :: ካልሆነ መንገዱን ጨርቅ ያግላቹ ነው የሚለው :: ባለፈው ምርጫ አዎ ተሳትፈናል ዓላማችን ህዝቡን ለማናሳሳትና ለመቀስቀስ ጠቅሞናል ::

ዳውድ:- ይህንን ህገ መንግሥት እንፈልገዋልን ::

ሀሰን :- ይህ የተነሳው ነጥብ በጣም ጠቃሚ ነጥብ ነው :: ዋናው ነገር ይህን ህገ-መንግሥት መቀበልና አለመቀበል ጉዳይ አይደለም :: ትግላችን ከበረታ ኢህአዴግ አይኖርም :: ሰለዚህ እሱን አስወግደን ህገ መንግሥቱን ልንገለገልበት ይገባናል :: አለበለዚያ ሊከተል የሚችለው ቀውስ ከባድ ነው የሚሆነው ::

ዳውድ:- ሱማሌን መመልከት ይቻላል ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንደሉ ::

አንዳርጋቸው ' ህገ መንግሥቱ አይደለም ችግሩ :: አገሩንም አንድ አፍርጎ የያዘው እሱ አይደለም :: ብዙ ነገሮች መለወጥ ያለባቸው ህጎች ይኖራሉ :: ህገ መንግሥቱን ራሱን የሚፈልጉ ወገኖች አሉ:: ቅንጅት ይህንን ተቀብለን ነው እየሰራን ያለነው:: ወደፊት የሚታይ ጉዳይ ይሆናል ::

ነገደ :- በዚህ ሰነድ ውስጥ የተጠቀሰው አንቀፅ 39 ብቻሳይሆን የሚያሳስቡን ብዙ ነገሮች አሉ መቀየር አለበት ::ይህ ህገመንግሥት ብለን ስንል:: ይህንን እስታሊናዊ ህገ-መንግሥት ተቀብሎ መሥራት ማለት ትራንዝሽናል አሬጅመንት የለም ማለት ነው የሚሆነው ::

ዶ/ር ስዮም ሰለሞን :- እባካችሁ ጊዜ አናባክን ይህንን መቀበል አለብን በህገመንግሥቱ ሥር እንቀሳሰቀስ ነው የምለው ::

ዳውድ' የሱዳንን ሁኔታ ተመልከቱ የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት አስወግዶ ህገ-መንግሥቱን ለመቀየር ነበር ግን አልሰራም ::

በዚህ ነጥብ ላይ ሁሉም ሲስማሙ ህገመንግሥቱ ን መቀበል በሚለው ዋነው መንግሥቱን ማስወገድ ብቻ ነው ሲሁ በበኅብረቱ ተወካዮች በኩል ህገ-መንግሥቱም አገዛዙ መቀየር አለባቸው በሚል በልዩነት ሀሳቡ ተጠቃልሏል::

አረገራዊ :- ሰለውክልናም ቢሆን ኅብረቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች አሉ :: ኅብረቱ እዚህ እንደምታዩት የአንድ ድርጅት ወኪል ሳይሆን በውስጡ አሥራ ሦስት ድርጅቶችን ያቀፈ ነው:: ስለዚህ አወካካሉ ሁሉ መታየት የሚገባው ጉዳይ ነው ነው የምንለው በእኛ በኩል ::

ከቅንጅቶችና ከኦነጎች በኩል በኅብረት ስም ነው የተጋበዛችሁትና ውክልናው በዛው መልክ ነው ሊሆን የሚችለው በሚል ሳይቀበሉት ቀርተዋል ::

ሌላው በኅብረቱ በኩል የተነሳውና ተቀባይነት ያላገኘው በኦነግ የተዘጋጁት ሰነዶችን በተመለከተ ከመጠሪያው (ርዕሱ) ጀምሮ መታረም ያለበት ነው

ለምሳሌ በኦነግ የቀረበው 1.Memorandum of Understanding for Freedom and Democracy የሚለው በ Memorandm of Understanding for Freedom and Understanding in Ethiopia በሚል መታረም አለበት የሚል ሀሳብ ቀርቦ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል መግባት የለበትም በሚል ተቃውሞ በኦነጎቹም ሆነ በሌሎቹ ተደግፎ ሲቀርብ ቅንጅቶቹም የረባ ተቃውሞ ሳያሰሙ የኦነጎቹን ሀሳብ ደግፈው ተቀብለዋል :: በሁለተኛው ሰነድ ላይ በዚሁ መልክ ውድቅ ተደርጓል:: ኅብረቱም በዙህ ላይም እንደማይስማመ ተነግሯቸዋል :: እንደውም ይህንን የምታነሱ ከሆነ ማለትም ኢትዮጵያ የሚለው ሥም ይግባ የምትሉ ከሆነ የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል የሚለው መግባት ይኖርበታል የሚል የማስፈራሪያ ሃሰብ ተደጋገሞ ከኦነግና ከስብስቦቹ ይሰነዘር ነበር ::

ዳወድ :- ኢትዮጵያ የሚለው ሥም ቢገባ በኦነግ ውስጥ ከፍተኛ ችግርን ይፈጥርብናል ::እዚህ ድረስ ሥንመጣ እዚህ ስብሰባ ላይ ሰንደርስ ቀላል አይደለም :: ብዙ መንገድ ተጉዘን ነው :: ስለዚህ ይህ ማለትም ኢትዮጵያ የሚለው ሥም

መውጣት አለበት ::

ኅብረቱ' እዚህ የተሰባሰብነው ኃይሎች አዲስና ዴሚክሲያዊት ሁሉንም በእኩልነት የምታስተናግድ አገር ለመገንባት ነው ና ኢትዮጵያ የሚለው ሥም መግባት ይገባዋል :: አለበለዚያማ አሽቸጋሪ ነው ::

ዳውድ' ስለኢትዮጵያ ታሪክ ብዙ ማለት ይቻላል ይሄ አይጠቀምም እናውራ ካልን መፀሃፍ የሚወጣው ታሪክ ልናወራ እንችላለን ::

ቅንጅቶች በኅብረቱ በኩል የተገፋትን የልዩነት ጥያቄን አልደገፉትም ::እንዳውም ችግር እንደሌለባቸው ነው አንዳርጋቸው ሳይቀር የገለፁት :: የአነጎችን ሀሳብ ተቀብሎ መሄድ ይሻላል በሚል ::

ሰለሞን በቀለ በመጨረሻ ላይ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ቢገባ ሜሞራንደም ኦፍ አንደርስታንዲጉ ላይ ጥሩ ነው ሲል ሃሳብ ሰነዘረ :: አንዳርጋቸው ስሙ አያጨቃጭንም የሚጠቅመውም ነገር የለም ሲል ሃሰብ ሰነዘረ ::

አብዱርቃድር ኦጋዴን:: ይሄ ነጥብ ማጨቃጨቅ የለበትም እኛም ኢትዮጵያ የሚለው ሥም ባይገባ ነው የሚሻለው የምንለው:: ለእኛ በጣም አስቸጋር ነው በሚል በስሜት ሀሳባቸውን ገልጠዋል ::

በመጨረሻም የኅብረቱ ተወካዮች በአጠቃላይ ኅብረቱ ወደዚህ ስብሰባ ጉባዔ ሲመጣ ይዞ የመጣውን አቋም በድጋሚ በማስረዳት ይህ ስብሰባ እንደ ፕሊምነሪ ወይም ቅድም ዝግጅት ማድረጊያ ተደረጎ እንዲወሰድ በማሰብ እንደነበር አመጣጣቸውን አጠንክረው ገለጡ :: በተጨማሪም ኅብረቱ በርካታ ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦች አላያንስ ለመፍጠር የሚያስችሉ እንዳሉት በተወካዮቹ ተገለጠ :: ስለዚህ የኅብረቱ ተወካዮች ከዚህ በላይ በኅበረቱ ተወካዮች በኩል ሊወሰድ የሚችል የአቋም ለውጥ ሰለሌ በሚቀጥሉት ውሳኔ የመስጠት ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ አችጋር መሆኑ ተገለጠላቸው ::በኅብረቱ በኩል ጉባዔውን አስመልከቶ ያለውን አቋም የሚገልፀውንና የተዘጋጀውን ሰነድ ለሁሉም ተሳታፊ ድርጅቶ ተባዝቶ ታደላቸው :: በአንድ ወር ጊዜ ውስጥም የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ወይም አመራሩ ተሰብስቦ ሀሳቡን እንደሚገልፅላቸው ተነገራቸው ::

ቅንጅቶች እኛ የተቀረነው እንቀጥል እነሱ በወር ጊዜ ውስጥ ያስታውቁን በሚል ሀሳብ አቀረቡ:: በወሰኑ ጊዜ ይቀላቀሉ በሚል ከቅንጅት ሌላ የማጠናከሪያ ሀሳብ ተሰጠ ::

በዚሁዕለት እሁድ ሜይ 21 ቀንከምሽቱ በ22:00 ሰዓት ማምሻውን በተካሄደው የሥራ ክፍፍል ምደባ ላይ ሳንሳተፍ ተሰነባብተን አቋማችንን አስስረግጠን ተለያየን::

13192561550

789173#